# በአማርኛ በትግርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች ለዊኪፔድያ፣ አስተዋፅኦ በማድረግ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ስለመረዳት

ሙሉ ሳይንሳዊ ፅሑፍ በሕሊና ሀይሉ ንጋቱ፣ ጆን ካኒ፣ ሳራ ቼሲንስ

ትርጉም በሀይሉ ንጋቱ

መስከረም ፳፻፲፮ ዓ.ም

This work is licensed under CC BY-NC-SA 4.0. To view a copy of this license, visit https://creativecommons.org/licenses/by-nc-sa/4.0/

ዊኪፔድያ፣ በዓለማችን በ300 ቋንቋዎች ከ191 በላይ ጥናታዊ ፅሁፎች የወጡበት ነጻ ኢንሳይክሎፒዲያ ለብዙ ጉዳዮች ላይ በርካታ መረጃዎች የሚሰጡበት የሚገኝበት የመረጃ ዘዴ ነው። የዊኪፒዲያ ተልዕኮ መግለጫ ማንኛውም የዚህች ፕላቴን ነዋሪ የሆነ ሰው የተጠቃለለ የሰው ልጅ ዕውቀት ያለምንም ገደብ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ይህ ቢባልም ግን ሁሉም የዓለም ቋንቋዎች በተመሣሣይ ሁኔታ ተወክለዋል ማለት አይቻልም።

በዲጂታል ሥርዓት ብዙ መረጃ የማይገኝላቸው ቋንቋዎች በአጠቃላይ ዝቅተኛ ምንጭ ያላቸው ቋንቋዎች በመባል ይታወቃሉ። በዚህ ምድብ ውስጥ የኢትዮጵያን ቋንቋዎች ጨምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ ቋንቋዎች ይካተታሉ። በዚህ ሥራ ናታችን ያተኮረው ከዊቢርዲያ ጋር በተያያዘ ከኦሮምኛ፣ ከአማርኛ እና ከትግርኛ ቋንቋዎች ጋር በተገናኘ በሚነሱ ችግሮች ላይ ይሆናል። እነዚህ ቋንቋዎች በራሳቸው አነስተኛ ምንጭ ያላቸው ሆነው በራሳቸው ቃል የማይገለፁ ቢሆንም የእያንዳንዱ ቋንቋ በዚህ ወረቀት ቀሪ ክፍል በስዕሉ እንገልፅዋለን ወይም በጠቅላላው የመረጃ አለመኖርን በሚያሳይ አገላለፅ እናስቀምጣለን። ይህንን ማድረግ ለቃሉ ዕውቅና መስጠትን ያስቀራልና የሕብረተሰብ ክፍሎች በራሳቸው ሁኔታ የራሳቸውን ቋንቋ ይጠቀማሉ የሚል ተስፋ አለን።

ብዙ መረጃ በሌላቸው ቋንቋዎች ለዊክፒዲያ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሰዎች የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመረዳት በዊኪፒዲያ መድረክ ውይይት የተደረገባቸውን መረጃዎች ለመተንተን የሚያስችለንን ጥናት አድርገናል፣ በትግርኛ ወይም በኦሮምኛ ወይም በአማርኛ ለመጻፍ የሞከሩ 14 ተሳታፊዎች አግኝተን አነጋግረናል። በዚህ ሁኔታ ባገኘነው ውጤት ላይ ተመስርተን አካታች የሆኑ ቴክኒዮሎጂዎችን ለመገንባት የሚያግዙ የዲዛይን ምክረ ሀሳቦችን በዚህ ፅሁፍ በተካተተ የግኝት መግለጫ አቅርበናል።


## ከአማርኛ ከትግርኛ እና ከኦሮሚኛ ቋንቋዎች ጋር በተያያይ የዊኪፒዲያ አሁናዊ ሁኔታ

በአጠቃላይ ሲታይ ዊኪፒዲያ ከተጠቀሱት ሶስት ቋንቋዎች አንጻር ከመጠንም፣ ከዓይነትና ወይም ከአግባብነት ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉበት ተረድተናል። በመሆኑም ከመጠን አንጻር በተጠቀሱት ሶስት ቋንቋዎች ያለው አስተዋፅኦ በጣም ሰፊ ክፍተት (ልዩነት) ያለበት መሆኑን ተረድተናል። ለምሣሌ በትግርኛ ቋንቋ የተዘጋጁ ፅሁፎች 304 ሲሆኑ ይህም በዐረብኛ ቋንቋ ከተዘጋጁ 650 ፅሁፎች ጋር ሲወዳደር መጠኑ ትንሽ ነው። እንደዚሁም በጣም የሚገርም ሁኔታ በተጠቀሱት ሶስት ቋንቋዎች የሚወጡ ፅሁፎችም በሥራ ላይ ያሉ ኦዲተሮች አንጻርም ሲታይ ከፍተኛ ምንጭ ካላቸው ተወዳዳሪ ቋንቋዎች ጋር ተገናዝቦ ሲታይ መጠኑ በጣም አነስተኛ ነው።


እንደዚሁም ዊኪፒዲያ የጥራት ችግርም እንዳለበት ተረድተናል። በተለይ ውስን መረጃ ካላቸው በስዕስለ “/ሀ/ ከተገለፁት የተመለከትነው በትግርኛ የተጻፈ የአንድ ፅሁፍ ስክሪንሽት በአንድ ግለሰብ ስም የኢትዮጵያ ታሪክ በሚል አርዕስት የተጻፈ ፅሁፍ ነው‹‹ በስዕል (ለ) ስር ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ የዊኪፒዲያ ፅሁፍ ሲሆን አርዕስቱም የኢትዮጵያ ታሪክ የሚል ነው። ትግራይ ውስጥ አንድ ከተማ ስለሚገኝበት አካባቢ የሚገልፅ ረዘም ባለ ዐ/ነገር ረዘምና ለየት ባለ ዐረፍተ ነገር የተዘጋጀ ነው። በዚህ ስንቀጥልም በተጠቀሱት ቋንቋዎች በዊኪፒዲያ የሚሰጡ ፅሁፎች በስዕል 2 ሥር የተገለፁት ቋንቋዎች የየራሳቸው ስዕል እንደሚያሳየው ባለአንድ ዓረፍተ ነገር ናቸው።ለ ንጽጽር ያህልም እና እንደምንረዳው በዐረብኛ ቋንቋ አስር የሚሆኑ ዓ/ነገሮች አሉበት። በተጨማሪ ለተጠቀሱት ሶስት ቋንቋዎች ከፍተኛው የዓረፍተ ነገር ብዛት በአንድ ፅሁፍ አስር ወይም መቶ ብቻ ሲሆን በዐረብኛ ቋንቋ ግን በአንድ ፅሁፍ በሺዎችና በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ዓረፍተ ነገሮች አሉት።




ስዕል 1 (ሀ) በትግርኛ ቋንቋ በዊሲፒዲያ ከወጣ አንድ ፅሁፍ የተገኝ፣





ስዕል 1(ለ) በአማርኛ ቋንቋ በዊሲፒዲያ ከወጣ አንድ ፅሁፍ የተገኘ





ስዕል 2. በአማርኛ፣ በትግርኛ ፣በኦረምኛ እና በዐረብኛ ቋንቋዎች በዊኪፒድያ የሚወጡ ፅሁፎች ዓ/ነገሮችን ስርጭት የሚያሳት ፕሎተር

ከእነዚህ ቋንቋዎች ጋር በተያዘ ዊኪፒዲያ የአግባብነት ጉዳይም አለው። ስዕል ለምሣሌ የአማርኛ ዊኪፒዲያ ዋና ገፅ ላይ በወጣ ፅሁፍ ላይ የሚታየው ስክሪንሽት ስላቢግ ማክኖልድ በርገር የሚገልፅ ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ፅሁፍ እየተጻፈ ባለበት ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ የማክኖልድ ሬስቶራንት የለም። በሌላ በኩል በኢትዮጵያ በጣም ስለተጠቀሰው አውራ አምባ የተባለው ማኅበረሰብ የኢትዮጵያ ባልሆኑ ስድስት ቋንቋዎች ፅሁፍ ወጥቷል።



(a) Amharic article about the Big Mac burger.




(b) English article about a famous community in Ethiopia.

ስዕል **3**፡ ስዕል 3/ሀ/ በአማርኛ የዊኪፒድያ፣ ዋና ገፅ ላይ ምንም እንኳ ኢትዮጵያ ውስጥ የማክዶላንድ ሬስቶራንት የሌለም ቢሆን አንድ ፅሁፍ ወጥቷል። በሌላ በኩል በስዕል 3/ለ/ ሥር የኢትዮጵያ ባልሆኑ 5 ቋንቋዎች ስለተጠየቀው አውራ አምባ ማኅበረሰብ ተፅፏል።


## ስለ አጠናን ዘዴ

ከላይ የተገለፀበት ሶስት ቋንቋዎች ዊኪፒዲን በተመለከተ ያለባቸው ጉድለት እንደተጠበቀ ሆኖ በዊኪፒዲያ በተጠቀሱት ቋንቋዎች የሚጻፉ ቋንቋዎች ተናጋሪዎች በኦንላይን የዕውቀት ምንጮች/ክምችቶች/ በሚሳተፉበት ጊዜ የሚያጋጥማቸው ችግሮች ምንድናቸው? የሚል የጥናት ጥያቄ አቅርበናል። ለዚህ የጥናት ጥያቄያቸው መልስ ለማግኘት ሁለት ጥናቶችን አድርገናል። በአንደኛው ጥናት በውይይት መድረክ ላይ የተነሱ መረጃዎችን ሰብስበናል። እንደዚሁም በዊኪፒዲያ ተሳታፊዎች የተወያዩባቸውን ችግሮች ለመረዳት ተሳታፊዎቹን በቀጥታ በማግኘትና በማነጋገር ጥናት ትንተና ሠርተናል። በተጠቀሱት ቋንቋዎች በዊኪፒዲያ የመሳተፍ ዕድል ዝቅተኛ ስለሆነ ወደዚህ መስክ ለመግባት ያለውን ፈተና መሰናክል ለመረዳት 14 አዲስ ተሳታፊዎችን በማግኘት ጥናት አድርገናል።

## ስለ ጥናታችን ግኝቶች

እነዚህን ጥናቶች ስናደርግ ዊኪፒዲያ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች ጋር በተያያዘ ያሉበትን ችግሮች በትክክል እናረጋግጣለን በሚል እሳቤ ነበር፣ የሆነው ግን በተለያ እና ነገር ግን ተያያዥ በሆኑ ከዊኪፒዲያ የተለያዩ ባህሪያት፣ የቋንቋ ድጋፍ መስጫ መሣሪዎች እና የማኅበራ ፖለቲካ ችግሮች ምክንያት ያገኘነው ውጤት ጥናቱን ስንጀምር ካሰብነው የተለየ ሆኖ አግኝተነዋል። ከዊኪፒድያ የተለየ ተፈጥሮ የሚመነጩ ችግሮች

1. የዊኪፒዲያ የተለየ ተፈጥሮ አንዳንድ ጊዜ በአገር ውስጥና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተቀላቀሉ መመሪያዎች ይመጣሉ ለምሣሌ በስዕል 4 የተመለከተው ሁኔታ ከተሳታፊዎች አንዷ የፐርሚሽን ስህተት ችግር እንደገጠማት ተረድተናል። ይህ የፐርሚሽን ስህተት በሚከተሉት ምክንያቶች ይህንን ገፅ መክፈት መፍጠር አትችልም የሚል ሲሆን ይህም የተገለፀው በትግርኛ እና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ነው።




ስዕል **4.** በትግርኛ ዊኪፒዲያ የተላለፈ በእንግሊዝኛ እና በትግርኛ ቋንቋዎች ቅልቅል የተጻፈ የፐርሚሽን ስህተት

2. በአገር ውስጥ ቋንቋዎች የቴክኒክና የሳይንስ ቃሎ በዊኪፒዲያ አለመጻፉ ሰዎች የተለመዱ አይደሉም። ተሳታፊዎቻችን በዋትሳፕ ፣ በሊንኮች ላይ የሰፈሩ ቃሎች ለመረዳትና ትክክለኛውን ሊንክ ለማግኘት ሲታገሉ ተመልክተናል። አንዳንዶቹ ተሳታፊዎቻችን ይህን ሁኔታ ቃሉ ከሌላ ቋንቋ ዲፕሉኬት ጋር አያይዘው ሲገልፁ ተመልክተናል። በተጨማሪም ተሳታፊዎች አንዳንዶቹ ውሎች በጣም ቃል በቃልና ወይም በዕለት ተዕለት ንግግር ጥቅም ላይ ያልዋሉ በመሆናቸው እንደሆነ አድርገው ይገልጻሉ።
3. በቀጥተኛ ቦታና በተገደበ ቦታ መረጃ ማግኘት አይቻልም። ተሳታፊዎቻችን በአንድ ፅሁፍ ላይ አንድ ስዕል ለመለጠፍን ጨምሮ አንዳንድ ድርጊቶችን ለማከናወን ከዊኪፒዲያ ውጭ መፈለግ ያለባቸው መሆኑን ተመልክተናል።

### የቋንቋ ድጋፍ ሰጭ መሣሪዎችን በተመለከተ

1. በግዕዝ ቋንቋ ዲጂታል መጻፍ አስቸጋሪ ነው፣ ተሳታፊዎቹ ሰባት ዓይነት የመጻፊያ ቦርዶች የተጠቀሙ ሲሆን ሁሉም በየራሳቸው ችሮች ገጥመዋቸዋል። የመድረክ ላይ ውይይቶችን ስንተነትን ያጋጠመን መሠረታቸው ላቲን በሆኑ ኪቦርዶች በግዕዝ ቋንቋ መጻፍ ጊዜ የሚበላ መሆኑን ተረድተናል።
2. በአሁኑ ጊዜ ከኦንላይን የዕውቀት ጥበቃ ነባር ልምዶች ጠፍተዋል። ተሳታፊዎች ታሪኮችና/ተረት ተረቶችን/ እና በልማድ ላይ የተመሠረተ ጥበቃ የተደረገላቸው የኦንላይን ዕውቀቶች ለመተው ፍላጎት ያላቸው መሆኑ ይታያል። የኦንላይን የዕውቀት ጥበቃን የተከተለ ጥበቃ የሆነ አጻጻፍ ዘዴ ስንመረምር እንደምንረዳት ማለት ነው።
3. በማሽን የሚደረግ ትርጉም መሣሪያዎችም ባህላዊ አግባብነት የሚጎድላቸው ሲሆን አድሎ የሚያስከትሉ እና በመጠኑም የተሳከረ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ተሳታፊዎችን የማሽን ትርጉም መሣሪያዎችን ሲጠቀሙ የመጨረሻ ውጤቱ ባህላዊ አግባብነት የሌለው መሆኑን ተገንዝበናል ለምሣሌ “ እህል ውኃችን አለቀ” ቃል በቃል እንደዚሁም የማሽን ትርጉም መሣሪያዎች የኢትዮጵያን የዘመኑን አቆጣጠር በተመለከተ አግባብነት ያላቸው በመሆኑም ለምሣሌ በሚሰጣቸው ትምህርት (ጊዜ) የተጻፈባቸው ፅሁፎችን ትርጉሙ ውጤት የትኛው የዘመን አቆጣጠር ጥቅም ላይ እንደዋለ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሲቀየር ስህተት ይፈጠርና በተለይ ፅሁፉ ታሪክን የሚመለከት ሲሆን ውጤቱ ጥሩ አይሆንም።

## ሶሲዮ ፖለቲካል ጉዳዮች

1. የሳይበር የፀጥታ እርጃዎች በቪፒኤን በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ገደብ አድርጓል፣ በሲፒኤና አማካይነት በዊኪፒዲያ የሚሳተፉ ሰዎች ቪፒኤን የሚጠቀሙት በፖለቲካ ምክንያት ነው፣ ብዙ ጥናቱ ተሳታፊዎቻችን ከቪፒኤን ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት በዊኪፒዲያ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ተገደዋል። ይህንን ፕሮግራም እያካሄድን እያለን የቴሌግራም ሆነ ዩቱዩብ የመሳሰሉት ማኅበራዊ ሚዲያዎች በኢትዮጵያ ከቪፒኤን ጋር በተገናኘ ሁኔታ አስተዋፅኦ ያደርጉ የነበሩ ተሳተፊዎቻችን አቋርጠዋል።
2. ስለማኅበረሰቦቹ የተጻፉ ምሁራዊ ፅሁፎች በጣም ውስን ሲሆኑ በተጠቀሱት ቋንቋዎች ምንም አላተረፈም ማለት ይቻላል። ተሳታፊዎቻችን ለሚያሚቸውን ፅሁፎች በማጣቀስ የሚጠቀሙበት ሳይንሳዊ ተመልክተናል፣ ፅሁፎቹ ለማግኘት ሲቸገሩ ተመልክተናል። በመጀመሪ ስለማኅበረሰቦቹ ምሑራዊ ምንጮች አለመኖር በአጠቃላይ ሁለተኛ ምንጮች ቢኖሩ እንኳ ያሉት በእንግሊዝኛው ወይም በሌላ የአውሮፓ ቋንቋ የተዘጋጁ ናቸው። ለምሣሌ አንድ ተሳታፊያችን ስለ አጼ ዮሐንስ የተጻፈ ፅሁፍ ዝርዝር ውስጥ ተመልክተነዋል እዩት የዓለም ሐሮልዶች ስብስብ ብቻ ነው ያለቸው ይህንን ሁኔታ ይገልጻል።
3. በዊኪፒዲያ አስተዋፅኦ ለማድረግ የገንዘብም ችግር አለ፣ ክፍያ ካልተፈፀመ በቋንቋቸው እውቀት ለመካፈልም ሆነ ስለማኅበረሰባቸው ለመጻፍ የማይሞክርና አስቸጋሪ መሆኑን ተገንዝበናል። እንደዚሁም በዊኪፒዲያ የሚወጡ ሕትመቶችን ማግኘትና አስቸጋሪ መሆን ከተሳታፊዎቻችን ተረድተናል። ስለውይይት መደረግ ባደረግነው ትንታኔ ላይ እንደተረዳነው በተሳታፊዎች አንዷ በቋንቋቸው አስተዋፅኦ ለማድረግ ይችሉ ዘንድ ከኢንተርኔት ጋር የተያያዘ በሞባይል ዳታ የመጠቀም ዕድል ስለሚገኝበት ሁኔታ አንስታለች።

## አካታች ቴክኒሎጂዎን ስለሚገኝበት/ስለመጠቀም/

ሀ) ስለዊኪፒዲያ የተለየ ተፈጥሮ ካጋጠመ ችግሮች ተነስተን የዊኪፒዲያ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች ለማቃለል የተለያዩ አማራጮችን ገልፀናል። ለምሣሌ ዊኪፒዲያ ፅሁፎች በቀጥታ ለመጫን ያስችለን ዘንድ ቋንቋን ለይቶ የማወቅ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በተቀላቀሉ ሁለትና ከዚያ በላይ ቋንቋዎች የተዘጋጁ ፅሁፎችን በተመለከተ ያሉትን ችግሮች ማቃለል ይቻላል። እንደዚሁም የተለየ የአካባቢ ዘዴ በመጠቀም በዊኪፒዲያ የፅሁፍ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ተሳታፊዎች በሌላ የተለየ ዘዴ የሚጽፉ ተሳታፊዎች የእነርሱን ዘየ እንዲጠቀሙ በማድረግ ድግግሞሽን ማስቀረት ይቻላል።

ለ) የማሽን ትርጉም አጥኚዎችም ለማሽን የትርጉም መሣሪያዎች መዋቅራዊ የሐሳብ ልውውጦች በማድረግ በፅሁፍ የሰፈሩ ቀኖችና ዓመታት ሳይለወጡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የፅሁፍ ታሪክ እንዳይለወጥ ማድረግ ይቻላል። እንደዚሁም በእነዚህ ቋንቋዎች ከትርጉም ጋር የተያያዘ ማኅበራዊ ወገንተኝነት እንዳይኖር ማድረግ ይቻላል።

ሐ) የግብዓት ሞዲሊቲስ የኦንላይን የዕውቀት ክምችቶችን በተመለከተ መሠረታቸው ላቲን በሆኑ የመጻፊያ ሰሌዳዎች ( keyboards) በተጠቀሱት ቋንቋዎች አውቶማቲክ የንግግር ማወቂያ ሥርዓት ለመጠቀም ዕድሉ እየመጣ ነው። በተጨማሪም ወደ ፅሁፍ መቀየር ሣያስፈልግ በቅድሚያ በቃል የተላለፈን ዕውቀት ለማካተትና ለመጠበቅ እንዲቻል በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን በድምጥ ሥርዓት መሠረት ሊደረግ የሚችል አስተዋፅኦ አለ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ፅሁፍ ዊኪፒዲያ ላይ በአማርኛ ፣በኦሮሚኛ፣ እና በትግርኛ መጻፍ ለተሳታፊዎች የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ተመልክተናል። ባደረግነተው ትንታኔ ላይ ተመስርተን አካታች የቋንቋ ቴክኔዎሎጂ ዕቅድ ዕድሎችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ምክረ ሀሳብ አቅርበናል። እንደ ዊኪፒዲያ ባሉ የኦንላይን የዕውቀት ማከማቻ አስተዋፅኦ ማድረግ ከፈለጉ በማኅበረሰብ አባሎች እና በቋንቋዎች ተናጋሪዎች ውሣኔ መሆን አለበት በማለት ፅሁፋችንን እንቋጫለን። በአሁኑ ጊዜ ለተለያዩ ቴክኒዮሎጂዎችና ሶስዮ ፖለቲካል ጉዳዮች ያሉን ዕቅዶች እንቅፋት አስተዋፅኦ ለማድረግ እንቅፋት እየሆኑብን ነው፣ ሥራችን ማኅበረሰቦች ለዊኪፒዲያ ወይም ለሌላ የዕውቀት ማከማቻ ክፍል አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው የሚል አቋም የለውም። ይልቁንም አካታች ቴክኒዮሎጂዎችንም ገንብተን እና አስተዋፅኦ የማድረግ ወይም ያለማድረግን ምርጫ ለቋንቋ ተናጋሪዎች እንተወዋለን።